


**ስለመልካም አገልግሎት የተበረከት ስጦታ፤**

ቱ.ማ.ኢ የፌዴራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የማኔጅመንት አባላት ለተቋሙ አመራሮች ስለ ውጤታማ ሥራቸው እና አገልግሎታቸው የጋቢ ሽልማት አበረከቱላቸው።



ኢንስቲትዩቱ ያገኘው እውቅና ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ የያዘችውን የከፍታ ጉዞ የሚያሳኩ ሰልጣኞችን በጥራት ለማፍራት ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል ተባለ።

መስከረም 9/2018 ዓ. ም

ቱ. ማ. ኢ

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዓለም አቀፍ የትምህርት ተቋማት ሥራ አመራር ሥርዓት 21001፡2018 እውቅናን አስመልክቶ የሥራና ክህሎትሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ሙፈሪሃት ካሚል ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢንስቲትዩቱ ዓለም አቀፍ የትምህርት ተቋማት ሥራ አመራር ሥርዓት 21001፡2018 ሰርተፍኬት ባለቤት መሆኑ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ የያዘችው የከፍታ ጉዞ የሚያሳኩ ሰልጣኞችን በጥራት ለማፍራት እና ቀልጣፋ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል ብለዋል።

ክብርት ሚኒስትር ኢንስቲትዩቱ ጥራት ያለው ስልጠና መስጠት የሚያስችለው የማሰልጠኛ ክፍሎች እና መሰረተ ልማቶች ማሟላቱን ጠቁመው የሚጠበቅበትን ሀገራዊ ተልዕኮ ይበልጥ መወጣት እንዲችል የማስፋፍያ ግንባታ በቅርቡ እንደሚጀምር ገልጸዋል።

ሰርተፍኬቱ የጥራት ሥራ አመራር ትግበራ ጅማሮ እንጂ መጨረሻ ባለመሆኑ ለአፍታም ቢሆን ወደኋላ መመለስም ይሁን መዘናጋት እንደማይፈቀድ አሳስበዋል።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙን ተከትሎ፣ መንግስት ለቱሪዝም ዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት፣ ኢንስቲትዩቱ ከማሰልጠን በላይ የሚለውን አዲሱን የዘርፉን እሳቤ በመላበስ ችግር ፈቺ በሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ ሰልጣኞችን በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የስልጠና ዘዴዎች በማሰልጠን፣ ዜጎችን ለሥራ ዓለም እያበቃ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተልዕኮውን በላቀ ደረጃ በመፈጸም የስልጠና አጠናቃቂዎቹን በተሻለ ሁኔታ ወደ ሥራ ዓለም እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ይረዳው ዘንድ ISO 21001:2018 የጥራት ደረጃን ከማረጋገጥ አንጻር በስልጠና፣ በምርምር እና በማማከር የሥራ መስኮች 467 የሚሆኑ ጥራት ስታንዳርዶችን ቀርጾ ሥራ ላይ መዋሉን ገልጸዋል።

በስነስርዓቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር መሰረት በቀለ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ ከምንላቸው ጉዳዮች መካከል የሰው ሃይል፣ መሰረተ ልማት እና የአሰራር ስርዓት ዋነኞቹ ናቸው ያሉ ሲሆን እነዚህ ተሰናስነው ከሌሎች ጠቃሚ ሁኔታዎች ጋር ሲዋሀዱ ትልቅ ለውጥ ያመጣሉ ብለዋል። የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲትዩትም ለዚህ ለውጥ የሚያግዙ የአሰራር ስርዓቶችን እያስተገበረ እንደሆነ ተናግረዋል።

ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ማዓዛ አበራ የእውቅና ሰርተፍኬቱ ለተቋሙ በመስጠት የጥራት ደረጃውን አስጠብቆ መሄድ እንዳለበት ተናግረዋል።

በመርሃ ግብሩ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት የተቋሙ አመራሮችና ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን ለሥራው መሳካት ጉልህ ሚና የነበራቸውን ተቋማትና የኮሚቴ አባላት የምስጋና ሰርተፍኬት ተበርክቶላቸዋል፡ ፡

ትክክለኛ መረጃዎችን ለማግኘት የሚከተሉትን ማስፈንጠሪያዎችን ይጠቀሙ




ክብርት ሙፈሪሃት ካሚል
"የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ተጠሪ ተቋም የሆነው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የዓለም አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ሥራ አመራር ሥርዓት ማረጋገጫ አግኝቷል።
ይህ ማረጋገጫ ኢንስቲትዩቱ ከዓለም አቀፍ ደረጃ ጋር የተጣጣመ የላቀ ሥልጠና፣ ምርምርና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችለዋል። በተጨማሪም ዜጎች ከተቋሙ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ፍትሐዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። " የሚል መልእክት አስተላልፈዋል።



ጥራት... ለልህቀት...

የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ተጠሪ ተቋም የሆነው የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የዓለም አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ሥራ አመራር ሥርዓት ማረጋገጫ አግኝቷል።

ይህ እውቅና ለኢንስቲትዩቱ ብቻ ሳይሆን፣ ለሀገራችን የክህሎት ልማትና የቱሪዝም ዘርፍም አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት ትልቅ ስኬት ነው።

ይህ ስኬት ኢንስቲትዩቱ ከዓለም አቀፍ ደረጃ ጋር የተጣጣመ የላቀ ሥልጠና፣ ምርምርና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችለዋል። በተጨማሪም ዜጎች ከተቋሙ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ፍትሐዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

እንደ ዘርፍ ለሥራው ልዩ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርን ጨምሮ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩትን እና የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን ጨምሮ ከ16 በላይ ተቋማት የዓለም አቀፍ የሥራ አመራር ስርዓት ማረጋገጫ ማግኘት ችለዋል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ አመራር የተጀመረው መንግሥት ለአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና እንዲሁም ለፈጠራና ፍጥነት የሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚያሳይ ነው።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አመራርና ሠራተኞች ለስኬቱ ላደረጋችሁት ርብርብ እንዲሁም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩትና የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በዘርፉ እያደረጋችሁ ላለው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ሙያዊ ድጋፍ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

የሥራ ባለቤት እርስዎ ነዎት!


ISO 21001
ECAE Certification
Tourism Training Institute


Ethiopian Conformity Assessment Enterprise Certification
CERTIFICATE
Educational organizations management system
TOURISM TRAINING INSTITUTE
ISO 21001:2018 Educational organizations
for the following activities
Effective date: 11 September 2025
Authorized by
Ethiopian Conformity Assessment Enterprise